በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የመገናኛ ዘዴዎች ተጽእኖ


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon@gmail.com


***<u>ቦታ፦</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ሐምሌ ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# የመገናኛ ዘዴዎች

- በማንኛውም መልክ መረጃን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ማድረስ የመገናኛ ዘዴ ይባላል፡፡

- መረጃን በርካታ ቁጥር ላላቸው ሰዎች ወይም ሕዝቦች ማዳረስ ደግሞ መገናኛ ብዙኀን ይባላል፡፡

- የመገናኛ ዘዴ ዓይነቶች፡-
    - ቴሌቪዥን (ኬብል፤ ኔትዎርክ፤ ሳተላይት፤ ዲሽ)
    - ራዲዮ (አይፖድ፤ ዎክማን)
    - ፊልምና ቪዲዮ (ሬንታልስ/ሙቪ/ሲኒማ)
    - የኅትመት ውጤቶች (ጋዜጦች፤ መጽሔቶች፤ ደብዳቤዎች…)
    - ፎቶግራፍ (ዲጂታል፤ ቪዲዮ ካሜራ)
    - ኤሌክትሮኒክ (ኢሜይል፤ ድራረ ገጽ፤…)

# ኢንተርኔት

- በዘመናችን በርካታ ሰዎች ኢንተርኔትን የመጠቀም እድል አላቸው፡፡

- በርካታ ወጣቶች ከማያውkቸው ምንጮች አስቸኳይ መልእክቶችን፤ ወይም ኢ-ሜይሎችን ይቀበላሉ፡፡

- ዕድሜያቸው ከ12-17 ያሉትም ሳይቀሩ ኢንተርኔት ይጠቀማሉ፡፡

- ወጣቶች ኢንተርኔትን የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ስንመለከት ኢንተርኔት ከ¹ደኞቻቸው፤ ከቤተሰቦቻቸውና ከትምህርት ቤታቸው ጋር ባላቸው ግኑኝነት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

- በርካታ ወጣቶች የሚሉት መረጃ እንደሚጠቁመው ወላጆቻቸው እንዲያዉቁት የማይፈልጉትን ነገር ሁሉ በኢንተርኔት በመጠቀም ይለዋወጣሉ፡፡

- ጥቂት የማይባሉ ወጣቶችም በቻት ሩሞች ወይም በአፋጣኝ የመልእክት ማስተላለፊያ መንገዶች በመጠቀም ከማያውkቸው ምንጮች መልእክት ይቀበላሉ ይወያያሉም፡፡

# ኢንተርኔት

- ጥቂት የማይባሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ስላራሳቸው ያላቸውን መረጃ (ስማቸውን፤ ዕድሜያቸውን፤ አድራሻቸውን፤ ፎቶአቸውን...) የማያውkቸው ሰዎች ይጠቀሙበት ዘንድ በመረጃ ድራረ ገጽ ላይ አኑረዋል፡፡

- ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉትም በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የሚማሩ ወጣቶች በመጀመሪያ በኢንተርኔት ከተገናኟቸው ሰዎች ጋር ፊትለፊት ለመገናኘት ችለዋል፡፡

- ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የሆኑ ወጣቶች በኢንተርኔት የሚያደርጉትን ነገር ከወላጆቻቸው ይደብቃሉ፡፡

- በዚህም ሂደት ልጆችና ወጣቶች በኢንተርኔት ለሚገኙ ልቅ የሆኑ የግብረ ሥጋ ድርጊቶች ወይም ወደነርሱ ላነጣጠሩ ሌሎች አደጋዎች ይጋለጣሉ፡፡

- በየመኝታ ክፍሎቻቸው ኮምፒዩተርና የኢንተርኔት አገልግሎት ካላቸው ወጣቶች ጥቂት የማይባሉት ፖርኖግራፊ ፊልሞችን ይመለከታሉ፤ በሕገ ወጥ ድርጊትም ተሳታፊ ይሆናሉ፤ እያደርም በቀላሉ ለዝሙት አዳሪነት፤ ለቦዘኔነትና ያለ ዕድሜመመቸውም ለመደፈር ይጋለጣሉ፡፡

# ቴሌቪዥን

- በርካታዎቻችን የቴሌቪዥን ባለቤቶች ከመሆናችን በተጨማሪ ቢያንስ በየቀኑ ከ3 ሰዓታት ላላነሰ ጊዜ ዘወትር ወይም አልፎ አልፎ ፤ ካልሆነም ፊልሞችን በመከራየት ወይም በመግዛት የምንመለከት ነን፡፡

- በዚህ ክፍለ ዘመን በርካታ ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ጋር ተገቢ የሆነ ውይይት ለማድረግ የሚወስዱት ጊዜ ቴሌቪዥን ወይም ፊልሞችን ለማየት ከሚወስዱት ጊዜ በብዙ እጥፍ ያነሰ ነው፡፡

- ልጆችም ቴሌቪዥን የማየት ወይም ከአባትና ከእናታቸው ጋር የመጫወት ምርጫ ሲቀርብላቸው በርካታዎቹ የሚመርጡት ቴሌቪዥን መመልከትን ነው፡፡

- ወጣቶች ቴሌቪዥን በማየት የሚያሳልፉት ጊዜ በትምህርት ቤትና በጥናት በድምር ከሚያሳልፉት ጊዜ ከሁለት እጥፍ በላይ ይበልጣል፡፡

- በርካታ ወጣቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት ነፍሰ ገዳይነትና አመጸኛ ድርጊቶችን ከቴሌቪዥን ይመለከታሉ፡፡ ጥቂት የማይባሉትም በቴሌቪዝን በሚመለከቷቸው የአመጽ ድርጊቶች ተስበው አመጸኝነት እንደሚያስደስታቸው ይናገራሉ፡፡

# <u>መገናኛ ዘዴዎች የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች</u>

1. **የቤተሰብ መበታተን፡-** *የሚገናኙበት ጊዜ ያጣሉ፣ ግኑኝነታቸውም ይቀንሳል፡፡*

2. **ለማያስፈልጉ ነገሮች መጋለጥ፡-** *አመጸኝነት፣ ልቅ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት፣ አደንዛዥ እጽ*

3. **እርስ በርስ የሚኖረው ለመግባባት የሚያስችሉ ብቃቶች ማነስ፡-** *የእርስ በርስ ግኑኝነት መቀነስ፣ ዓይን ለዓይን መተያየት አለመቻል*

4. **የመጥፎ ተጽእኖዎች መፈጠር፡-** *በሐሳብ፣ ምራል፣ በስሜትና በጠባይ…*

5. **በጤንነት ላይ የሚያስከትለው አደጋ፡-** *እንቅስቃሴ የተዳከመበት የሕይወት ገጽታ፣ የጀርባና የአንገት ቅርጾች መጣመምና በአጠቃላይ የቁመና መበላሸት፣ የሕይወት ቀውስ፣ …*

6. **ጊዜን ያለአግባብ ማጥፋት፡-** በሬድዮ ሙዚቃ፣ *በቪዲዮ ጌሞች፣ በተለያዩ ፊልሞች፣ በሞባይል ስልክ ልቅ ወሬ በማውራት፣ ጠቃሚ ሳልሆኑ ጋዜጦች ከሚገባው በላይ ጊዜ በመስጠት፡፡*

# እግዚአብሔር ምን ይላል?

*ጌቶች ናችሁ ወይስ ባሮች? ይላል፡፡*

- የሚቆጣጠራችሁ ማነው? የተቆጣጠራችሁስ ምንድር ነው?
- #እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።; *ዘፍጥ 1:28፡፡*
- #ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥ በጎችንም ላሞችንም ሁሉ ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፥ የሰማይንም ወፎች የባሕርንም ዓሦች፥ በባሕር መንገድ የሚሄደውንም ሁሉ።; *መዝሙር 8:4-8፡፡*
- #ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።; *1ኛ ቆሮ 6:12፡፡*

*በሰጠኋችሁ ነገርስ ታምናችሁ ተገኝታችኋል? ይላል፡፡*

- በሰጠኋችሁ ጊዜ፤ ጤና፤ ሀብታና ንብረት፤ ችሎታ ታምነናችኋል?
- #ጌታውም። መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።; *ማቴ 25:23፡፡*

# እግዚአብሔር ምን ይላል?

- “ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። እግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ። ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል። እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን።” *1ኛ ዮሐ 4:1-6።*

- “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” *ሮሜ 12:2።*
- “በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ።” *ፊል 4:8።*

# እግዚአብሔር ምን ይላል?

- “ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።” *1ኛ ዮሐ 2፡15-16።*
- “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” *ዮሐ 3፡16።*

- “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።” *ማቴ 6፡24።*
- “ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።” *1ኛ ዮሐ 5፡3።*

- “በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና” *1ኛ ጴጥ 5፡8።*
- “የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!” *ማቴ 622-23።*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።